አዲስ ቻምበር ADDIS CHAMBER | 75 1947-2022 | ይቻላል It's Possible! | Open For Ad

# ንግድና ልማት

ግንቦት / ሰኔ 2016 እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com

## የቤይጂንግ ኢትዮጵያ የቢዝነስ ትብብር ጉባኤ በአዲስ አበባ በተሳካ ሁኔታ ተካሂዷል



**አዲስ ቻምበር፤ ሰኔ 14 2016 ኢ.ም)** እ.አ.አ በ1970ዎቹ መጀመርያ ላይ ይፋዊ የዲፕሎማሲ ግንኙነት የጀመሩት ኢትዮጵያና ቻይና የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብሮችን በመፈራረም በአቅም ግንባታ፤ በድህነት ቅነሳና በመሳሰሉ ዘርፎች ላይ በመስራት በርካታ አመታትን አስቆረዋል:: ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ ቻይና የኢትዮጵያ ዋና የልማት አጋር በመሆን በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ በመሰማራት ላይ ትገኛለች::

ለዘመናት የዘለቀው የሁለቱ ሀገራት የንግድና የኢንቨስትመንት ግንኙነት አንድ አካል የሆነው የቤይጂንግ ኢትዮጵያ የቢዝነስ ትብብር ጉባኤ በአዲስ አበባ በተሳካ ሁኔታ ተካሂዷል:: በቤይጂንግ ቻምበር ኦፍ ኢንተርናሽናል ምክር ቤት እና በቤይጂንግ አለምአቀፍ ንግድ ጉባኤ ከአዲስ ቻምበር ጋር በጋራ በመሆን የተዘጋጀው የንግድ ጉባኤ በርካታ የቻይና እና የኢትዮጵያ የንግድ ኩባንያዎች በአንድ መድረክ ያገናኘ ሲሆን የንግድ ለንግድ ትስስሮች ፤ የመግባቢያ ሰነዶች የተፈረሙበት መድረክ ነበር:: ከነዚህ የትብብር ፊራሚዎች መካከል አዲስ ቻምበር ከቤይጂንግ አለምአቀፍ ንግድ ምክር ቤት ጋር ያደረገው ስምምነት ተጠቃሽ ነው::

በዚህ ጉባኤ ላይ ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች ንግግር ያደረጉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ ሀሰን መሃመድ፣ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ሰመሪታ ሰዋሰው፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የመካከለኛው ምስራቅ፣ ኢዥያና ፓስፊክ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄኔራል አምባሳደር ገበየሁ ጋንጋ (ዶ/ር)፣ የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መሰንበት ሸንቁጤ፤ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዚደንት መላኩ እዘዘው እንዲሁም የልኡካኑ ቡድኑ አባላት ይገኙበታል::

የቻይና ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸው የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የገለጹት የአዲስ ቻምበር ፕሬዚደንት መሰንበት ሸንቁጤ በተለይም የቻይና ኩባያዎች በተለያዩ የግንባታ ፕሮጀክቶች መሰማራታቸው የስራ እድል እንዲፈጠር እና የመሰረተ ልማት ፍላጎት እንዲሻሻል ማድረጋቸውን ገልጸዋል::



አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

በአዲስ አበባ ንግድና
የዘርፍ ማኅበራት
ምክር ቤት እየተዘጋጀ
የሚወጣ ጋዜጣ

፶ኛ ዓመት እትም

ADDIS BUSINESS

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirmamecha@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
ከፍያለው ዋሲሁን
ካሳሁን ማሞ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ስዩም ጫኔ-ሰብሳቢ
ካሳሁን ማሞ - አባል
አሸናፊ ምትኩ - አባል
አቶ ደሳለኝ ደጀን - አባል
አቶ የሀንስ ወ/ገብርኤል - አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
ግንቦት / ሰኔ 2016 እትም

# ርዕሰ አንቀጽ

## የታክስ አሠራርን እና አተገባበርን ቀልጣፋ በማድረግ የንግድ ተወዳዳሪነትን እውን እናድርግ!

የንግዱ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ውስጥ የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ለማናችንም ግልጽ ነው:: በስራ ዕድል ፈጠራ፣ የመንግስትን ገቢ እና የውጭ ምንዛሪን በማሳደግ፣ የሀገሪቱን ጥቅል ምርት እንዲጨምር በማድረግ ረገድ አስተዋፅኦው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ማምጣቱን የምንገነዘበው ጉዳይ ነው::

በዚህ ረገድ የሀገር ውስጥ ገቢ በብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ገንቢ ሚና ካላቸው እንቅስቃሴዎች አንዱና ዋነኛው ነው:: ጠንካራና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ ለመገንባትና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን ለማስፈን የተረጋጋና ጤናማ  የሆነ የግብር ስርአት መኖር ወሣኝነት አለው ብለን እናምናለን:: ግብር ለከተሞችም ቢሆን ለመሰረተ ልማት እድገታቸው የጀርባ አጥንት እንደሆነ ለማናችንም ግልጽ ነው::

የግብር ጉዳይ ለአንድ ሀገር የህልውና ምሰሶ ነው:: ሀገራት እንደ ሀገር መቀጠል ካለባቸው ተገቢውን ግብር መሰብሰብ እና የተሰበሰበውን ግብር በአግባቡ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማዋል እንዳለባቸውም ይታመናል::

በእርግጥ ግብር መክፈልም መንግሥት አስቻይ የፍትሕ ሥርዓትን ለማስፋት፣ ሰላምንና ፍትሐዊ የግብር ሥርዓትን ለማስፈን ያስችላል ብለን እናምናለን:: ይሁን እንጂ በግብር ዙሪያ የሚወጡ አዋጆችና ደንቦች ከመውጣታቸውም በፊት ሆነ ከወጡ በኋላ የሚመለከታቸውን አካላት በሚፈለገው ልክ የማያሳትፉና በግንዛቤ ማስጨበጥ ዙሪያ ክፍተት ሲታይባቸው ይስተዋላል::

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ከሰሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት 16 በመቶ አንጻር ስትታይ በግብር መልክ የምትሰበስበው ከ10 በመቶ ያልዘለለ መሆኑ ገና የግብር መሰረቱ ያልሰፋ መሆኑን ያሳያል:: የዚህ መንስኤ ደግሞ በውስጥና በውጪ ምክንያቶች ሳቢያ ውስብስ እንደሆነ እናምናለን::

በእርግጥ የታክስ አስተዳደሩ የታክስ አሰባሰብ ቅልጥፍና ችግር፤ የታክስ ፖሊሲ ክፍተት፤ የህብረተሰቡ ግብርን የመክፈል ባህል አናሳ መሆን፤የመረጃ አሰጣጥ ችግር፤የሰው ሀይል እና የቴክኖሎጂ ክፍተቶች ለታክስ መቀነስ በምክንያትነት የሚነሱ ናቸው:: ይህ በሀገሪቱ የታክስ ገቢ በሚፈለገው መጠን እንዳያድግ በማድረግ የፋይናንስ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ መፍጠሩን ምክር ቤቱ ይረዳል::

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የታክስ አሠራር እና አተገባበር ቀልጣፋና ለንግድ አሰራር አስቻይ እንዲሆን አሁን ያለው የታክስ ፖሊሲና ሕግ፤ መመሪያ ወደፊት ከሚታሰበው የግል ዘርፉ ሚና አኳያ መቃኘት ይኖርበታል::

በታክስ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲሁም በልዩ ልዩ የግብር ነክ ጉዳዮች ላይ የንግዱ ህብረተሰብና መንግስት የሚወያዩባቸውን የግንኙነት መድረኮች ችግሮች ስር ሳይሰዱ ቶሎ የመቀረፍ እድሉን በማግኘት መፍትሄዎቹንም በጋራ ለማፈላለግ ከገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤትና ከባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ መስራቱ ጠቃሚ ይሆናል ብለን እናምናለን::

ይህንን ችግር ለመቅረፍ ደግሞ የንግድ ምክር ቤታችን ከህግ አውጪውም ይሁን ከአስፈጻሚው አካል ጋር አብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ለመግለጽ ይወዳል::

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# የአዲስ ቻምበር ዋና ፀኃፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም በቻይና የዓለም አቀፍ ንግድ ማስተዋወቅ የቢይጂንግ ንኡስ ምክር ቤት የተመራ የንግድ ሉኡክን ተቀብለው አነጋገሩ




**በከፍያለው ዋሲሁን**

የኢትዮ- ቤጂንግ የቢዝነስ ትብብር ማስፈፊያ ጉባኤ ቀደም ብሎ የሁለቱ አገራት የንግድ ምክር ቤቶች ንግድና ኢንቨስትመንት በሚጠናከርበት ሁኔታ ላይ ግንኙነት መክረዋል:: አቶ ሺበሺ በሰጡት ገለፃ አዲስ ቻምበር የሀገሪቱ 60 በመቶ ጥቅል አመታዊ ምርት ( GDP ) የምታወጣው አዲስ አበባ የከተማ ንግድ ምክር ቤት ነው ብለዋል:: አክለውም ምክር ቤታቸው ከ17ሺ አባላት ያሉት አንጋፋና ጠንካራ ተቋም ከመሆኑም በላይ የንግዱን ማህበረሰብ ችግር በአድቮኬሲ ፖሊሲ አማካኝነት ችግሩ እንዲፈታ የሚሰራ ምክር ቤት መሆኑንም ጠቅሰዋል::

የኢትዮ -ቻይና ግንኙነት ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑን አቶ ሺበሺ ጠቅሰው ፤ ግንኙነቱ ወደ ንግድና ኢንቨስትመንት በማደግ በርካታ የቻይና ኩባንያዎች በኢትዮጵያ መዋለ ንዋያቸውን አፍሰሰዋል ብለዋል::

የቻይና ኩባንያዎች በግንባታ እንዲሁም ኢንቨስትመንት ዘርፎች መሰማራታቸውን ጠቁመው ፤ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠራቸውንም ነው የገለፁት::

በመሆኑም ሌሎች የቻይና ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው መዋለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ አዲስ ቻምበር ያበረታታል ፤ ለዚያም ይሰራል ብለዋል :: በሁለቱ አገራት መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን የጠቀሱት አቶ ሺበሺ ፤ ባለፉት አስራ አንድ አመታት 88 ቢሊየን ዶላር የሚያወጣ የንግድ ልውውጥ አድርገዋል ብለዋል::

ይህም በያመቱ በአማካይ የ5 ቢሊየን ዶለር እድገት እያሳየ መምጣቱን ገልፀዋል:: ያም ሆኖ የንግድ ሚዛኑ ወደ ቻይና ያደላ እንደሆነ የምክር ቤቱ ዋና ጸሀፊ ገልጸዋል:: በቻይና የዓለም አቀፍ ንግድ ማስተዋወቅ የቢጅንግ ንኡስ ምክር ቤት ምክትል ሊቀመንበር ዉ ላን በበኩላቸው ምክር ቤቱ እ.ኤ.አ በ1978 ዓ.ም መቋቋሙን ገልፀዋል :: ዓለማውም ዓለም አቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንትን በቤይጂንግ ለማስፋፋት መሆኑን ጠቅሰው አዲስ አበባ የመጡት ከኢትዮጵያዊያን ነጋዴዎች ጋር አብሮ ለመስራት እና አጋርነት ለመፍጠር ነው ብለዋል:: የኢትዮ- ቤጂንግ የቢዝነስ ትብብር ማስፈፊያ ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ ከመጡ ኩባንያዎች መካከል በኤሌክትሪክ መኪና አምራች ኩባንያ ፣ ኤክስሬይንና መሰል የህክምና ቴክኖሎጂዎችን የሚያመርት ፣ የግብርና ቴክኖሎጂ የተሰማሩ ኩባንያዎች ይገኙበታል:: አዲስ ቻምበርና የቻይና ዓለም አቀፍ ንግድ ማስተዋወቅ የቢይጂንግ ንኡስ ምክር ቤት የመግባቢያ ሰነድ እንደሚፈራረሙ ለማወቅ ተችሏል::

# የአዲስ ቻምበር ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አቻዎቻቸው ጋር ተወያዩ



በማላቦ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የክብር ቆንስላ የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ በሃይሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳይሬክቶሬት ጄኔራል የመካከለኛው አፍሪካ ዴስክ ተጠሪ የሆኑት ወ/ሮ መስከረም ሽፈራው ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት በመገኘት የሁለቱን ሀገሮች የንግድና ኢንቨስትመንት ለማሳደግ በኩባንያዎች መካከል ግንኙነት መፍጠር ስለሚቻልበት፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ ኩባንያዎች በኢኳቶሪያል ጊኒ ስላለው የኢኮኖሚና ቢዝነስ ዕድሎች መረጃ ስለሚያገኙበት ፣ እንዲሁም ላኪዎች ለውጪ ገበያ የሚያቀርቧቸው ምርቶችና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው የንግድ ም/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አድርገዋል::

በውይይቱ ላይ አቶ ሥዩም ጫኔ የአዲስ ቻምበር ም/ዋና ፀሐፊ- አባላትና ግንኙነት ስለ ንግድ ምክር ቤቱ አጠቃላይ ገለፃና በኢትዮጵያና ኢኳቶሪያል ጊኒ መካከል ባለፉት አመታት በገቢና በወጪ ንግድ ዙሪያ የተከናወኑ የንግድ ግንኙነቶችን የተመለከተ መረጃ አቅርበዋል::
በማላቦ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የክብር ቆንስላ የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ በሃይሉ በበኩላቸው ለኢትዮጵያዊያን ባለሀብቶች በኢኳቶሪያል ስላሉት የቢዝነስ ዕድሎች ሰፊ ማብራሪያ ከመስጠታቸውም በተጨማሪ የሀገራችን ኩባንያዎች በተለይም በውጪ ንግድ መስክ ተጠቃሚ ሊሆኑባቸው የሚችሉ መስኮች ብዙ መሆናቸውን ገልፀዋል:: በተለይም በግብርና ፣ በስጋ ፣ በማዕድን ፣ በፋይናንስ ፣ በአየር ትራንስፖርትና በትምህርት መስኮች ገና ያልተነኩ ዘርፎች በመሆናቸው የሁለቱንም ሀገራት ባለሃብቶች የሚያገናኙ መድረኮች በቀጣይ መፍጠር እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል:: በመጨረሻም የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ጋር መረጃ በመለዋወጥ በጋራ በመወያየትና ቀጣይ ዕቅዶችን በመንደፍ የተጀመረውን ግንኙነት ለማሳደግ እንደሚሠራ ለክብር ቆንስሉ ተገልፆላቸዋል::

በማላቦ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የክብር ቆንስላ የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ በሃይሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳይሬክቶሬት ጄኔራል የመካከለኛው አፍሪካ ዴስክ ተጠሪ የሆኑት ወ/ሮ መስከረም ሽፈራው ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት በመገኘት የሁለቱን ሀገሮች የንግድና ኢንቨስትመንት ለማሳደግ በኩባንያዎች መካከል ግንኙነት መፍጠር ስለሚቻልበት፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ ኩባንያዎች በኢኳቶሪያል ጊኒ ስላለው የኢኮኖሚና ቢዝነስ ዕድሎች መረጃ ስለሚያገኙበት ፣ እንዲሁም ላኪዎች ለውጪ ገበያ የሚያቀርቧቸው ምርቶችና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው የንግድ ም/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አድርገዋል::
በውይይቱ ላይ አቶ ሥዩም ጫኔ የአዲስ ቻምበር ም/ዋና ፀሐፊ- አባላትና ግንኙነት ስለ ንግድ ምክር ቤቱ አጠቃላይ ገለፃና በኢትዮጵያና ኢኳቶሪያል ጊኒ መካከል ባለፉት አመታት በገቢና በወጪ ንግድ ዙሪያ የተከናወኑ የንግድ ግንኙነቶችን የተመለከተ መረጃ አቅርበዋል::

በማላቦ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የክብር ቆንስላ የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ በሃይሉ በበኩላቸው ለኢትዮጵያዊያን ባለሀብቶች በኢኳቶሪያል ስላሉት የቢዝነስ ዕድሎች ሰፊ ማብራሪያ ከመስጠታቸውም በተጨማሪ የሀገራችን ኩባንያዎች በተለይም በውጪ ንግድ መስክ ተጠቃሚ ሊሆኑባቸው የሚችሉ መስኮች ብዙ መሆናቸውን ገልፀዋል:: በተለይም በግብርና ፣ በስጋ ፣ በማዕድን ፣ በፋይናንስ ፣ በአየር ትራንስፖርትና በትምህርት መስኮች ገና ያልተነኩ ዘርፎች በመሆናቸው የሁለቱንም ሀገራት ባለሃብቶች የሚያገናኙ መድረኮች በቀጣይ መፍጠር እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል::

በመጨረሻም የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ጋር መረጃ በመለዋወጥ በጋራ በመወያየትና ቀጣይ ዕቅዶችን በመንደፍ የተጀመረውን ግንኙነት ለማሳደግ እንደሚሠራ ለክብር ቆንስሉ ተገልፆላቸዋል::

# አዲስ ቻምበር “ለዲጂታል አገልግሎት ሰጪዎች የፋይናንስ ተደራሽነትን ማሳደግ በሚል የመንግስትና የግል ዘርፍ የምክክር መድረክ በአዲስ አበባ አካሂዷል

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከአለም አቀፉ የግል ኢንተርፕራይዝ ማእከል ጋር በመተባበር “ለዲጂታል አገልግሎት ሰጪዎች የፋይናንስ ተደራሽነትን ማሳደግ በሚል የመንግስትና ግል ዘርፍ የምክክር መድረክ አካሂዷል ።

የምክክር መድረኩን በንግግር የከፈቱት የአዲስ ቻምበር ዋና ፀሃፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም እንደተናገሩት ምክር ቤቱ በግሉ ዘርፍና በመንግሥት መካከል እንደ አገናኝ ድልድይ ሆኖ ከሚያከናውናቸው ሥራዎች መካከል ለግሉ ዘርፍ አመቺ የሆኑ ህጎችና ፖሊሲዎች እንዲወጡለትና ተግባራዊ እንዲሆኑለት ጥረት ማድረግ ነው ብለዋል፡፡

ምክር ቤቱ ምቹ የንግድ ከባቢ ሁኔታ ፣አመቺ አሰራሮችና ፖሊሲዎች እውን እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡ የግሉ ዘርፍ በግንባር ቀደምትነት ካስቀመጣቸው ለቢዝነስ ፈታኝ ከሆኑ




ጉዳዮች መካካል የብድር አቅርቦት አለመኖር ከፍተኛውን ድርሻ መያዙን በመድረኩ ላይ ጠቁመዋል፡፡
ንግድ ምክር ቤቱም ራሱን በዘመናዊና በዲጂታል ቴክኖሎጂ ታግዞ ለአባላቱና ለግሉ ዘርፍ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን በመድረኩ ላይ ተናግረዋል፡፡ በመድረኩ ላይ የተገኙትና የቁልፍ ንግግር ያደረጉት የአለም አቀፉ የግል ዘርፍ ኢንተርፕራይዝ ማእከል የምስራቅ አፍሪካ ዳይሬክተር አቶ ሀይለመለኮት አስፋው እንደተናገሩት የግሉ ዘርፍ እድገት ማነቆ ተብለው ከተዘረዘሩት መካከል ከመሬት አቅራቦትና ከግብር በመቀጠል የብድር አቅራቦት ዋነኛው መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ይህም የግሉ ዘርፍ አዳዲስ ምርት ለማምረትና ተወዳዳሪ እንዳይሆን ተግዳሮት መሆኑን አስረድተዋል ፡፡

በምክክር መድረኩ የተለያዩ ጽሁፎች የቀረቡ ሲሆን ከአቅራቢዎቹ መካከል በኢፌዲሪ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከፍተኛ አማካሪ የሆኑት ዶ/ር ካሊድ አህመድ፣ የአሸዋ ቴክኖሎጂ መስራችና ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ዳንኤል በቀለ እና የቴክኖቢዚያ ኢንዱስትሪያል ዴቨሎፕመንት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ለሚ ቱጆ ይገኙበታል፡፡
በአዲስ ቻምበር የተዘጋጀው የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የጋራ የውይይት መድረክ ዋና አላማ በፋይናነስ አቅርቦት ዙርያ የዲጂታል አገልግሎት ሰጪዎች የሚጋጥማቸውን ተግዳሮት በሚመለከታቸው አካላት የፖሊሲ ምላሽ እንዲያገኝ ግፊት ማድረግ ነው፡፡

# ወደ አመራርነት መምጣት የቻሉ ሴቶች ተተኪ ለማፍራት ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው ተገለጸ

**በሰናይት እሸቱ**

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በቀርቡ ባቋቋመው የዳይሬክተሮች ተቋም አማካኝነት በአመራርነት ላይ ላሉ የዳሽን ባንክ ሴት ሰራተኞች ለሶስት ቀኝ የቆየ ስልጠና ሰጥቷል፡፡



ስልጠናው ሴቶች የአመራር አቅማቸውን ማጎልበት እና ወደተሻለው መምጣት እንዲችሉ የሚያግዝ እና የአመራር ምንነትን ሴቶች ወደ አመራነት ለመምጣት እንቅፋት በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር ውስጣዊ እና ውጫዊ እንቅፋቶችን ለመቀነስ ወደ ራስ ተመልክቶ እራስን ማብቃት እንዴት ይቻላል በሚለው ላይ እንዲሁም በአመራርነት ቦታ ላይ የሚጠበቀውን ለማበርከት እና ውጤታማ ለመሆን ስሜቶቻችንን እንዴት ነው የምንገታው የሚሉት ርዕሶች ትኩረት አግኝተዋል፡፡

ስልጠናውን ከሰጡት ባለሞያዎች መካከል ወ/ሮ አስቴር አስፋው እንዳሉት ሴቶች የአመራርነት እድሉን ለማግኘት ብዙ ውጣ ውረዶችን እንደሚያልፉ እና እድሉንም ካገኙ በኋላ ከተጽዕኖ ለመላቀቅ ስለሚቸገሩ ተተኪ ለማፍራት እንቅፋት እንደሚገጥማቸው አንስተዋል፡፡

ሴቶች ወደ አመራርነት ቦታ ላይ ከመጡ በኋላ ስራዎቻቸው ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ ሁለት ሶስት እጥፍ ስራዎችን እንዲያከናውኑ የሚጠበቅባቸው መሆኑ ካለው የአመለካከት ችግር ምክንያት የመጣ መሆኑን ያነሱት አሰልጣኟ ይህ ችግር ሴቶች ውጤታማነታቸውን ለማሳየት በሚለው እሳቤ አጠቃላይ የህይወታቸውን ሚዛን ጠብቀው ለመኖር እንዳይችሉ እንደሚያደርጋቸው አንስተዋል፡፡
ይሁን እና ግን ሴቶች ያላቸውን አቅም እና የስራ ውጤታማነት ሌሎች እንዲያቁላቸው ለማድረግም ሆነ ተቀባይነት ለማግኘት የራስን አቅም ማሳደግ እና ማጎልበት መፍትሄ እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡

የስልጠናው ተሳታፊዎችም እንዳሉት ሴቶች ወደ አመራርነት ለመምጣት ከሚያልፏቸው እንቅፋቶች ባልተናነሰ አመራር ከሆኑ በኋላ ስራዎቻቸው ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚገጥማቸው ፈተና የጠነከረ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን ይህንንም አሸንፎ ውጤታማ ለመሆን የሚከፍሏቸው ዋጋዎች እንደሚበዙ አንስተዋል፡ ከነዚህም መካከል ከስራ ሰአት ውጭ እንዲሰሩ መገደድ፣ ስራዎችን መኖርያ ቤት ድረስ ይዞ ሄዶ መስራት፣ የራስን የህይወት ሚዛን በሚያዛባ መልኩ ከሚጠበቅባቸው ቁጥር በላይ መስራት የሚሉትን እንደማሳያ ጠቅሰዋል፡፡

ሴቶች ከስራ ባሻገር ያሉትን የህይወት ዘርፎች አመጣጥነው እና ደስተኛ ሆነው መኖር እንዲችሉ የአመራርነት አቅማቸውን የሚያሳድጉ እንዲሁም በተቋማት ውስጥም ሆነ በማህበረሰቡ የአመለካት ለውጥ ለማምጣት ሴቶች ላይ ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ያቀፈ ስልጠናዎች እንደሚያስፈልጉ ያነሱት ደግሞ ሌላኛዋ አሰልጣኝ ወ/ሮ እቴነሽ ተስፋ ሲሆኑ ያሉትን እንቅፋቶች ተቋቁመው ወደ አመራርነት መምጣት የቻሉ ሴቶች በትኩረት ሊሰሩበት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ የአመራነትን ቦታ የያዙ ሴቶች የሴቶችን ችግር የማወቅ እድላቸውን ተጠቅመው የተለያዩ ችግሮቻውን ሊፈቱ የሚያስችሉ ስራዎችን ሊሰሩ ይገባልም ብለዋል፡፡

# የአለም ንግድ ድርጅትና ያልተቋጨው የኢትዮጵያ የአባልነት ጥያቄ

**በሙሉጌታ ጉደታ**

የአለም ንግድ ድርጅት፣ ወይንም በእንግሊዝኛው World Trade Organization በምህፃረ ቃሉ (WTO) ተብሎ የሚታወቀው በአለም መንግስታት ይሁንታ የተመሰረተ ድርጅት ሲሆን አላማውም በአባል አገራት መካከል የሚካሄደውን የንግድ ግንኙነት ወይም እንቅስቃሴ ማቀላጠፍ ነው:: እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1995 እንቅስቃሴውን የጀመረው ይህ ድርጅት የተመሰረተውም አስቀድሞ የነበረውን የታሪፍና የንግድ አጠቃላይ ስምምነት ወይም General Agreement on Tariffs and Trade (GATT) የተባለውን 164 አባል አገራትን አቅፎ የነበረውንና በ1948 የተመሰረተውን ድርጅት በመተካት ነው::

ኢትዮጵያ በፈረንጆች አቆጣጠር 2003 ላይ የዚሁ ድርጅት አባል ለመሆን በይፋ ጥያቄ ካቀረበችና እንቅስቃሴ ከጀመረች 20 አመታትን ያህል አስቆጥራለች:: በእርግጥ የዚህ ድርጅት አባል መሆን እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ላሉ አገሮች የሚያስገኛቸውን ጥቅሞችና የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች በተመለከተ በወቅቱ አያሌ ይፋቱና ይፋቱ ያልሆኑ ውይይቶች ተካሂደዋል:: አያሌ ስብሰባዎችም በአብዛኛው በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አነሳሽነት ሲካሄዱ እንደነበር ይታወሳል:: የነዚህ ውይይቶች አላማም በንግዱ ማህበረሰብና በመንግስት አካባቢ ግንዛቤ ለመፍጠር ያለመ እንደነበሩ ይታወሳል::

በወቅቱ ምክር ቤቱ አያሌ የንግዱ ማህበረሰብ ጎምቱ የሚባሉ አባላትንና አመራሮችን እንዲሁም ምሁራንን ለውይይት በመጋበዝ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶት እንደነበር የሚታወስ ነው:: ምንም እንኳን በወቅቱ የነበረው መንግስት የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ጥቅሞች በተመለከተ ቁጥብነት ያሳይ የነበረ ቢሆንም ምክር ቤቱ ግን ተስፋ ሳይቆርጥ ጥረቱን ቀጥሎበት ነበር::

ይህ ጥረት በረጅም ሂደት እያደገ መጥቶ ነው በአሁኑ ጊዜ አገራችን የአለም ንግድ ድርጅት አባል እንድትሆን በአጠቃላይ ፍላጎትና ስምምነት በመንግስትም ሆነ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አካባቢ ሊፈጠር የቻለው:: እ.ኤ.አ በ2012 አካባቢ በአገራችን የተፈጠረውን ለውጥ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የማሻሻያ መርሃ ግብር አመቺ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው የአለም ንግድ ምክር ቤት አባልነት ጉዳይም እንደዚሁ ነፍስ ዘርቶ እንደገና አጀንዳ መሆን ጀምሮ እንደነበር ይታወሳል:: ይህ ሲባል ግን ኢትዮጵያ የድርጅቱ አባል ብትሆን የኢኮኖሚ ችግሮች ወዲያውኑ ይፈታሉ ብሎ ስለታሰበ አልነበረም:: የድርጅቱ አባልነት ጥያቄ ከመጠን በላይ የተጓተተ ከመሆኑም በላይ አስቀድመው አባል የሆኑ ታዳጊ አገሮችም በድርጅቱ አሰራር ላይ ተደጋጋሚ ቅሬታዎች ሲሰነዝሩ ተስተውለዋል:: እንዲያውም አባል ከመሆን አባል አለመሆን ይሻላል ወደሚለው ያዘነበለ አስተሳሰብም ነበር::

ያም ሆነ ይህ ግን የአለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን ለሁሉም ችግር የመጨረሻ መፍትሄ ይሆናል ማለት አይደለም:: ችግሮች በውይይት መፍትሄ እንዲያገኙ አመቺ ሁኔታዎችን ሊፈጥር ይችላል እንጂ በአንድ ጀንበር ችግሮችን በአጠቃላይ ያስወግዳል ማለት አይደለም:: ስለሆነም የድርጅቱን ችግር የመፍታት አቅም ሳያሳንሱም ሆነ ሳያጋንኑ መገምገም ያስፈልጋል:: አለበለዚያ ግን በተስፋ ፋንታ በድርጅቱ ላይ ተስፋ የመቁረጥ አዝማሚያ ሊፈጠር ይችላል:: ለዚህም ነው በአባልነት ዙሪያ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ በተለይ ታዳጊ አገሮች ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ጠንክረው መከራከርና የሚበጁ ሃሳቦችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል የሚባለው:: በእርግጥም የአለም የንግድ ድርጅት በአለም አቀፍ ንግድ ዙሪያ ክርክርና ውይይት የሚደረግበት ብቸኛ መድረክ ነው:: ዋነኛው ተግባሩም የአለም አቀፍ ንግድ ፍሰት በተቻለ መጠን ችግር እንዳይገጥመው ሊገመትና ሊሻሻል የሚችል ማድረግ ነው::

የአለም ንግድ ድርጅት ቢያንስ አምስት ቁልፍ አላማዎች አሉት:: መጀመሪያ አላማው የአለም አቀፍ ንግድ ህጎች ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው:: ሁለተኛው አላማው ተጨማሪ የንግድ እንቅስቃሴዎች በግሉ ሴክተር አማካይነት በነፃነት እንዲካሄዱ የምክክር መደረክ መፍጠር ነው:: ሶስተኛው አላማው በአለም አቀፍ ንግድ ዙሪያ ለሚነሱት አለመግባባቶች በህጉ አግባብ መፍትሄ እንዲያገኙ መርዳት ነው:: አራተኛ አላማው የውሳኔ አሰጣጡን ሂደት ግልፅ ማድረግ ሲሆን አምስተኛው አላማው ደግሞ ከሌሎች አለም አቀፍ የንግድ ተቋሞች ጋር ተባብሮ መስራት ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ድርጅቱ አምስት መርሆዎችን ይከተላል:: እነሱም፣ የአድልዎ አሰራር አለመኖር፣ የእርስ በርስ መስተጋብር፣ ሊተገበሩ የሚችሉና ግልፅነት ያላቸውን አሰራሮች መከተል ናቸው::

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ፣ የአለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን ጥቅሞችም ተግዳሮቶችም አሉት:: ጥቅሞች የሚባሉት የንግድ እንቅስቃሴዎች በታሪፍ ቅነሳ አማካይነት እንዲሳለጡ ማድረግ ነው:: የንግድ ክርክሮች በአግባቡ እንዲፈቱ ህጋዊ ማእቀፍ መፍጠር፣ በአገራት መካከል የሚካሄደው ንግድ ያለአድልዎ እንዲካሄድና ስምምነቶች ከአድሏዊ አሰራር ነፃ እንዲሆኑ መርዳት፣ እንዲሁም ነፃ ንግድን ማስፋፋት ናቸው:: ተግዳሮቶች ናቸው የሚባሉት አሰራሮች ደግሞ ለታዳጊ አገሮች ተስማሚ ያልሆኑ የንግድ ህጎችን ማውጣትና ታዳጊ አገሮች ታዳጊና ጥቃቅን የንግድ ድርጅቶቻቸውን አግባብነት ከሌለው ውድድር መጠበቅ እንዳይችሉ ወይም ከለላ እንዳያደርጉ ማድረግ ነው:: ሌላውና መጨረሻው ተግዳሮት በአለም አቀፍ ንግድ ዙሪያ የሚካሄዱት ስምምነቶች አስቸጋሪና የጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ ውስብስብ ሁኔታዎችን ለማለፍ መገደዳቸው ነው::

ለረጅም ጊዜ በተደጋጋሚ የሚካሄዱት የድርጅቱ የአባልነት ጥያቄም ሆነ ሌሎች ጉዳዮች ብዙ አመታትን ከማስቆጠራቸውም በላይ እጅግ አዝጋሚ መሆናቸውም ይጠቀሳል:: ብዙዎቹም ያለአንዳች ስምምነት እንደቀጠሉ ናቸው:: በተለይ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ለንግድ ከለላ የሚወጡ ህጎች አሜሪካንና የአውሮፓ ህብረት አባል የሆኑትን ያደጉ አገሮችን እንጂ ታዳጊ አገሮችን አይጠቀሙም ተብለው ይተቻሉ:: በተጨማሪም ድርጅቱ ከሚተችባቸው ጉዳዮች አንደኛው በተለይ ለትላልቅ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች የሚጠቅሙ ህጎችና ያወጣል ተብሎ ነው::

ኢትዮጵያ የአለም አቀፍ ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ከ20 አመታት በላይ ድርድር ላይ እንደቆየች ይነገራል:: የድርቱ አባል በመሆንና ባለመሆን ዙሪያ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ አገር አያሌ ውይይቶችና ክርክሮች ሲካሄዱ ቆይተዋል:: እነዚህ ውይይቶች እንዲጀመሩም ሆነ እንዲቀጥሉ የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከፍተኛውን አስተዋፅኦ ሲያደርግ ቆይቷል ቢባል ነገሩን ማጋነን አይሆንም:: በንግድ ምክር ቤቱ ጥረትም በግሉ ሴክተርና በመንግስት መካከል የተቀናጀ አሰራርና መግባባት እንዲሰፍን የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል:: በተጨማሪም ምክር ቤቱ አያሌ ምሁራንና በጉዳዩ ያገባናል የሚሉ ወገኖችን በማስተባበር የምክክር መድረኮችን አስተናግዷል::

ድርጅቱ በጃንዋሪ 30-2020 ባደረገው የአባል አገራት ስብሰባ ወቅት የኢትዮጵያ የአለም ንግድ ድርጅት የአባልነት ጥያቄ በተሳታፊ አገሮች ዘንድ ሙሉ ለሙሉ አዎንታዊ ምላሽ እንዲያገኝ ሆኗል:: ይህም ስብሰባ ጉዳዩን በተመለከተ ከስምንት አመታት በኋላ የተደረገ የመጀመሪያው ስብሰባ ነበር:: በዚያን ወቅት የኢትጵያ ልኡካን ቡድን እንዳስታወቀው ከአባል አገራት ጋር ተባብሮ በመስራት የአገራችንን የአባልነት ሂደት በፈረንጆች አቆጣጠር 2021 ላይ እንዲጠናቀቅ ተስማምቶ ነበር::

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

# ጥቂት ሰለ ቻይና ቤልት አንድ ሮድ ኢኒሼቲብ (RBI)


**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

በእንግሊዝኛ ስያሜው የቻይና የቤልት አንድ ሮድ ኢኒሽየቲቭ በምዕጻሩ ደግሞ BRI /ቢ.አር. አይ/ በመባል ስለሚታወቀው የቻይና አሕጉር አቋራጭ እና 148 አገራትን ስለሚያስተሳስረው ግዙፍ ገበያ መሠረተልማት ዘመቻ በአካባቢያዊ እና በዓለም ንግድና ኢኮኖሚ ሥርዓት ላይ ያለው ተጽዕኖ የብዙዎችን ቀልብ የሳበ እና ያነጋገረ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል:: ይኸው የቻይና በተለይ በአፍሪቃ ለአገራችን ይዞ የመጣውን ዕድል እና ፈተና የባለሙያዎችን አስተያየት ልናስነብባችሁ ወድደናል::

አስር አመታትን ያስቆጠረው የቻይናው ቤልት ኤንድ ሮድ ፕሮጀክት ለሁላችንም በቀላል አማርኛ እንዲገባን ከሆነ ቻይና አውሮጳን ሰንጠቀው የሚያልፉ ሁለት መንታ የሆኑ የየብስ እኛ የባቡር የንግድ መስመሮችን እንዲሁም የአፍሪቃን፤የደቡብ አሜሪካ፤ የመካከለኛው ምሥራቅና እና የደቡብ እስያ አገራትን ለማስተሳሰር የባሕር መስመሮችን በመዘርጋት የቻይናን ገቢ እና ወጪ ንግድ ከዓለም አገራት ጋር ለማስተሳሰር ያዘጋጀችው ውጥን ነው ሲሉ የቢዝነስ ልማት ባለሙያው አቶ ዳዊት ኃይሌ ይናገራሉ:: ቻይናዎች ያኔ በጨለማው ዘመን አባቶቻቸው ያስቀመጡትን አሻራ የአገራቸውን ዕድገት ለማስቀጠል ተቀብለው በዛሬው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የአገራትን ንግግድ የማስተሳሰር ዘመቻ ወይም ፕሮጀክት ነው ነው ይላሉ::

የፕሮጀክቱ ዓላማ ቻይና በቢሊየን የሚቆጠር ዶላሮችን በማፍሰስ አገራቱን እርስ በርስ ለማስተሳሰር የባቡር ሃዲዶችን፤አውራ ጎዳናዎችን፤ አዳዲስ ወደቦችን መገንባት እና ነባሮችን ማስፋፋት እንዲሁም እነዚህ አገራት በቴሌኮሚኒኬሽን እና በሳይበር ቴክኖሎጂ ማስተሳሰር ነው::

መዳረሻው ደግሞ እነዚህ የንግድ መስመሮች በመሠረተ ልማት እና በቴክኖሎጂ ከየአገራቱ ጋር በትብብር በመገንባት ሰላማዊ እና አስተማማኝ የንግድ መሥመር መፍጠር ነው:: መነሻውን ከአውሮጳ ቤልጂየም አድርጎ




በሩሲያ ሞስኮ ፤በኢስታምቡል ቱርክ አልፎ በፓኪስታን አቋርጦ ወደ ቻይና ዘልቆ በሺያን ከተማ ያበቃል:: ሁለተኛው መሥመር የባሕር ሲሆን ከቤልጂየም የባሕር ወደቦች ተነስቶ በጣልያን እና በግሪክ ወደቦች አድርጎ፤ ቀይ ባሕርን አቋርጦ ወደ ጅቡቲ እና ኬንያ ሞምባሳ ወደብ ይደርሳል:: ከዚያም የሕንድ ውቅያኖስን ሰንጥቆ በኢራን፤ በስሪላንካ፤ በኢንዶኔዥያ፤በማሌዥያ እና በቬትናም (ሃኖይ) ወደብ ይደርስና መዳረሻውን በቻይና ጓንዡ ወደብ ያደርጋል::

የቻይና የሲልክ /የሐር ንግድ መሥመር እየተባለ የሚታወቀው ጥንት ቻይናውያን እንደ አፍጋኒስታን፤ ካዛክስታን፤ ቱርክሚኒስታንን ሕንድ እና ፓኪስታን አቋርጦ የሚሄድ በመካከለኛው እስያ አድርጎ እስከ ካዛኪስታን አውሮጳ ድረስ ዘልቆ የሚሄድ የንገድ መሥመር ሲሆን ለአገሪቱ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አዳዲስ የንግድ መዳረሻዎችን ያስገኘላት ፕሮጀክት ነበር::

ከክርስቶስ ልደት በፊት 200 አመት ገደማ በሃን ነገሥታት የተጀመረው የንግድ መስመር የቻይናን የሐር፤የቅመማቅም ምርቶች ለአገሪቱ የንግድ መዳረሻ ያቀኑት የንግድ መሥመር ሲሆን አዲሱ RBI ሃሳብ የተጸነሰው የአሁኑ የቻይና ፕሬዝደንት እ.አ.አ መስከረም 2013 ዓ.ም ካዛኪስታንን በጎበኙበት ጊዜ ነበር:: በአመቱ ዕቅዱ ይፋ ሆነ:: ቻይናን ጨምሮ በአጣቃላይ 148 አገራት ማለትም 18 የአውሮጳ ሕብረት እና የቡድን 20 አገራት በርካታ የአፍሪቃ፤ የደቡብ አሜሪካ የመካከለኛው እና የሩቅ ምሥራቅ እንዲሁም የእስያ ፓሲፊክ አገራት መግባቢያ ሰንድ ፈርመዋል:: አገራችን ኢትዮጵያም እ.ኤ.አ በ2018 ዓም ተፈራርማለች :: ቻይና ለዚህ 60 ሺሕ ኪሎሜትር የሚያካልለውን የንግድ መሥመር መሠረተ ልማት ግንባታ ብቻ ወደ 125 ቢሊየን ዶላር ወጪ አድርጋለች::

ቻይናውያን ይህንን ሲያስቡ አሁን ዓለም የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ደረጃ ከምግት ውስጥ በማስገባት በርካታ አገራትን የየብስ እና የባሕር ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማስታጠቅ መስመሮቹ የደሩ ገበያዎች ማድረግ ነው ሲሉ ይሰማሉ:: ሌሎቹ ደግሞ በ2ኛው ጦርነት ማግሥት አሜሪካን የምዕራብ አውሮጳ አገራት ኢኮኖሚ እንዲያገግም ያደረገችውን የማርሻል ፕላን ጋር ያገናኙታል:: በዚህም በቻይና ፊታውራሪነት የሚዘወር አዲስ የዓለም ገበያ ሥርዓት ይፈጠራል ሲሉ ሥጋታቸውን ይሰነዝራሉ:: የሆነው ሆኖ ከመሐል ሆነው የሚታዘቡት ደግሞ ጊዜው ገና ጠዋት ስለሆነ ዝምታን መርጠዋል:: BRI ፍጹም የፖለቲካ ጠረን የሌለው እና ቻይና ከፍተኛ ገንዘብ አውጥታ ሙሉ ለሙሉ በቢዝነስ ላይ የተመሠረተ ነው የሚሉ ወገኖች ደግሞ በሌላ በኩል ቆመዋል:: አንዳንዶቹ በተለይ ለአፍሪቃ፤ለላቲን አሜሪካ እና እስያ አገራት ቀደም ሲል የዓለም ንግድ ሥርዓት ሆኖ ከቆየው እና በምዕራባውያን ድሃ አገራት ምርት አቅራቢ ሃብታሞቹ ደግሞ ዋጋ ቆራጭ ከነበሩበት የንግድ ዘይቤ የተለየ እና ሁሉም ለሁሉም ጋር የተሳሰረ አቅራቢ እና ሁሉም ከሁሉም ተቀባይ የሆነ ገበያ እንደሆነ የቻይና ዓለማቀፍ የጥናት ተቋም አውሮጳ ተመራማሪ ቺ ሆን ዢያን ይነገራሉ:: ቺ ሆን ዢያን የቻይና ዓለማቀፍ ኢንስቲቲዩት ባልደረባ እንደሚሉት መካከልኛው ምስራቅ እስያ ለቻይና ትልቁ የአውሮጳ በር ነው:: ከ16 አገራት ጋር በመንግድ በየብስና በባሕር ለመተሳሰር ችለናል:: ምክንያቱም አንዚህን አገራት መጀመሪያ በማስተሳሰር ወደ ምሥራቅ በመጓዝ የአውሮጳ ገበያን በጋራ ለመድረስ ያስችለናል ይላሉ:: በነገራችን ላይ እኛም ለእነዚህ አገራት የምንልከው እና የምናስገባው በተፈጠረው የየብስ ኔትወርክ ነው:: ለምሳሌ ከኡዝቤክትታን የጫነው ባቡር በአካባቢው ኤክስፖርት አድርጎ ሲመለስ ያው ባቡር የገቢ ምርቶችን ይጭኖ ይመለሳል ማለት እንችላለን:: ስለዚህ እነዚህ አገራት በቀላሉ እርስ በእርስ የንግድ ልውውጣቸውን ያለ ጣልቃ ገብነት ያከናውናሉ:: አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ በተዘረጋው የትራንስፖርት አማራጭ ወጪ እና ገቢ ንግዳቸውን ተሻግረው ወደ 3ኛ አገር ጋር ማከናወንም ይችላሉ ሲሉ የፕሮጀክቱን የጋራ ጠቃሚነት ይሞግታሉ::

ወደ አፍሪቃ ስንመለስ የኢኒሼቲቡ 2ኛው አካል ደግሞ ቻይናን በባህር መሠረተ ልማቶችና ትራንስፖርቶች ወደ ደቡብ ምሥራቅ እስያ፣ በመቀጠልም ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እና አፍሪቃ አገሮችን የሚያስተሳስር ነው:: ይኸው ኢኒሼቲቭ በህንድ ውቅያኖስ ዙሪያ የሚገኙ አገሮችንም ጭምር የሚያስተሳስር ስለሆነ ኢትዮጵያ፣ ኬንያና ጂቡቲም አሉበት:: የፕሮጅክቱ ወጪ እና የገቢ ንግዳቸውን በተለይ ኤክስፖርት ንግድ የሚጠይቀውን የመንገድ፤ የሎጂስቲክስ፤ የቴሌኮም፤ የሸቀጦች ማከማቻ አንደ ኢትዮጲያ ላሉ ወደብ የሌላቸው አገራት ጭምር ፋይዳው የበዛ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ:: የቀድሞ የአፍሪቃ ሕብረት ኮሚሽን ም/ሊ/መንበር ኤራስተስ ሙዌንቻ የዚህ ሀሳብ አንዱ አራማጅ ሲሆኑ የዛሬ 10 አመት ግድም የተጀመረው የቢአር አይ ኢኒሼቲቭ ለአፍሪቃ አገራት ትልቅ ዕድል ሆኖ በብዙ ዘርፎች መሻሻልን ያመጣ ፕሮጀክት ነው ይላሉ ::

አንድ ነገር በአጭሩ ላንሳ ይላሉ

## ጥቂት ሰለ ቻይና ቤልት ...

ሚ/ር ሙዌንቻ ፡፡ የአፍሪቃ አገራት ሁሉም ከዓለም ንግድ ድርሻቸው እዚህ ግባ የሚባል አይነት አይደለም፡፡ የዓለም ንግድ ወድድር ሩጫ ላይ ጭራ ሆና የምትገኘው አፍሪቃ አንድ መሠረታዊ ጉድለት ስላለባት ነው፡፡ የአፍሪቃ አገራት በመሠረተ ልማት እጅግ ወደ ኋላ ቀርተዋል፡፡ ለንግዳቸው ማሳለጫ የሆነው መሠረተ ልማት ጉድለት ቻይና እየሞላችው ነው፡፡ ይህ ዕድል በራሱ ትልቅ የንግድ ማነቃቂያ ግብዓት ይሆናቸዋል፡፡ የአፍቃ አገራት እንደ ሃይል ምንጭ፤የእርሻ፤የማዕድን ወዘተ ቦታዎች እና የወደብ፤የባቡር የአየር መስመሮች ለዘመናት ሳይተሳሰሩ ቆይተዋል፡፡ በነገራችን ላይ በዚህ ፕሮጀክት በአፍሪቃ ወደ 3000 ፕሮጀክቶች ተጀምረዋል፤ ለብዙ ወጣቶች የሥራ ዕድል አስገኝቷል፡፡ ቻይና በመሠረተ ልማት ለአፍሪቃ አገራት ያደረገው ድጋፍ ከዚህ ቀደም በዓለም ባንክና በሌሎች አበዳሪዎች ካደረጉት ድጋፍ እጅግ የበዛ እንደሆነ ይነገራል፡፡

በንግድ ዓለም አትራፊ ሆኖ መውጣት አንዱ የቢዝነስ እውነታ ነው፡፡ በዚያው ልክ የአፍሪቃ እና የቻይና ጓደኝነት ያለአቻ ጋብቻ እንዳይሆን ብዙዎች ይሰጋሉ፡፡ ለአፍሪቃ አገራት እንደ አንደ ፈተና ሆኖ የሚነገርለት ጉዳይ ደግሞ ቻይና የአፍሪቃ ትልቋ የንግድና ኢንቨስትመንት ባለድርሻ ብትሆንም የንግድ ሚዛኑ ያጋደለው ለቻይና ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በሁለቱ መካከል በሚደረገው ንግድ አትራፊዋ ቻይና ናት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የዘርፉ አዋቂዎች አፍሪቃ አንዳትጎዳ መሪዎቿ ሃላፊነት አለባቸው ሚሉ ወገኖች ደግሞ የነገውን በጥርጣሬ የሚያዩቱ ናቸው፡፡

የዓለማቀፍ ስትራተጂክ ጥናት ማዕከል ተመራማሪ የሆኑት ጀምስ ክራብትሪ በበኩላቸው የወጪ ንግዳቸውን ለማሳደግ ትልቅ ፈተና ለሆነባቸው የአፍሪቃ፤ የደቡብ እስያ አገራት መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ ስለዚህ አሁን ላይ በተዘረጉት መሠረተ ልማቶች አማካኝነት ንግዳቸውን ለማነቃቃት እንደሚያስችላቸው ይናገራሉ፡፡ በእኔ እይታ ይላሉ ዶ/ር ክራብትሪ ፤ይህ የቻይና አገራትን በንግድ መስተሳሰር ፕሮጀክት እስያን፤የደ/ምሥራቅ እስያ አገራት አፍሪቃ እና የላቲን አሜሪካ አገራትን ያካልላል፡፡ ይህ እኒሽየቲቭ ቻይናን ብቻ ሳይሆን ቀና ቀና ማለት የጀመሩትን ታዳጊ ኢኮኖሚዎች በብዙ ያነቃቃል፡፡ በነገራች ላይ ቻይና ለአመታት የገነባችው ሰፊ ግንብ የተበጣጠሰ የንግድ ትስስር በአንድ ጅረት እንዲፈስሱ ለማድረግ ያደረገችው ዕቅድ ይመስላል፡፡

የምሥራቅ አፍሪቃ አገራትን በተመለከተ ቻይና ለኡጋንዳ፤ለግብጽ እና ለኢትዮጵያ የነዳጅ ማስተላለፊያ እና ለባቡር መንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ የፋይናንስ ድጋፍ አድርጋለች፡፡ በኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ ጂቡቲ ወደብ ድረስ 753 ኪ.ሜ የተዘረጋው እና በኬንያ ከናይሮቢ ሞምባሳ ወደብ የሚያገናኘው የፈጣን ባቡር መንገድ ፕሮጀክት ኢትዮጵያን፤ኬንያን እና ጂቡቲ በዚህ የንግድ ሰንሰለት የሚያስተሳስረው ዕቅድ አካል ነው፡፡

የንግድ ልማት ባለሙያው አቶ ዳዊት እንደሚሉት ያገራችን ኤክስፖርተሮች በዕድሉ በስፋት እንዲሳተፉ መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻዎች ድጋፍ ማድረግ አለባቸው ሲሉ ምክረሃሳባቸውን ይሰነዝራሉ፡፡

የንግድ ልማት ከፍተኛ ባለሙያው አቶ ዳዊት አሁን ላይ ዲዛይን ሆኖ እየተሰራ ያለው ቤልት አንድ ሮድ ኢነሺየቲቭ እንደ መቀነት ኢትዮጵያን ኮኔክት የሚያደርገው በበቡር የተገናኘው ኢትዮ-ጂቡቲ የባቡር መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ የእኛ አገር ነጋዴዎች በተለይ ለኤክስፖርተሮች በጣም የሚመረጠው የሚደገፈው ኤክፖርት ነው፡፡ ኤክስፖርተሮች በአፍሪቃ ነጻ የንግድ ገበያ የተፈጠረውን ዕድል ማየት አለባቸው፡፡ በእኛ አገር የሚያቅተን ይኸው ነው ይላሉ፡፡ የሚያቅተው እዚህ ላይ መንግሥት የነጋዴውን ሕብረተሰብ ተወዳዳሪ የማድረግ እና አስፈላጊ የሆኑ አስቻይ የቢዝነስ ፖሊሲዎችን ክለሣ በማድረግ የንግድ ምሕዳሩን ማዘመንና ቀልጣፋ የማድረግ ሥራ ከመንግሥት ይጠበቃል ሲሉ ምክረ ሃሳባቸውን ይሰነዝራሉ፡፡

## የአለም ንግድ ድርጅትና ያልተቋጨው...

ከ ገጽ 5 የዞረ

የኢትዮጵያ የአባልነት ጥያቄ ድጋፍ ባገኘበት በዚያን ወቅት አንዳንድ ሃገሮች ካቀረቡት የድጋፍ ሃሳብ መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡ “ኢትዮጵያ የድርጅቱ አባል ለመሆን የምታደርገውን ጠንካራ ግፊት፣ እንዲሁም ይህንን ተከትሎ ሂደቱ እንዲፋጥን አገሪቱ በምታሳየው ፍላጎት መሰረት በአባልነት ጥያቄ ዙሪያ አምስተኛ ስብሰባ እንዲካሄድ የስብሰባው ሊቀመንበር አረጋግጠዋል” ይህም ሆኖ ግን የአገራችን የአባልነት ጥያቄ እስከዛሬ ድረስ እልባት ሳያገኝ ሲንከባለል ቆይቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ ኢትዮጵያ ፍላጎታቸውን ከሚያሳዩ አገራት ጋር የገበያ እድልን የማስፋፋት የሁለትዮች ውይይቶችን እንድታካሂድ ጥሪ ደርሷት ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ የድርጅቱ አባሎች ሃሳባቸውን እንዲሁም አስተያታቸውን በፅሁፍ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው እንደነበር ይታወቃል፡፡እስካሁን ግን ያስገኘው ጥቅም በተጨባጭ የሚታይ ሊሆን አልቻለም፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን በአገሮች መካከል እያደገ ከመጣው የንግድ ልውውጥ ኢትጵያን የመሳሰሉ ታዳጊ አገሮች ያገኙት እዚህ ግባ የሚባል ጥቅም እንደሌለ በሰፊው ይነገራል፡፡ ታዳጊ አገሮች ለአለም ንግድ የሚያዋጡት በመጠን ሲሰላ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ታዳጊ አገሮች የአለምን 20 ከመቶ የሚሆን የህዝብ መጠን ያላቸው ሲሆን፣ በአለም አቀፍ ንግድ ያላቸው ድርሻ ግን ከ0.03% በታች ነው፡፡

ምንም እንኳን የአለም ንግደ ድርጅት ለሁሉም አባል አገራት ተመሳሳይ ጥቅሞችን ለማስገኘት የሚሰራ መሆኑን ደጋግሞ ቢናገርም ተጨባጭ እንቅስቃሴው ግን ባደጉ አገሮች ፍላጎት አንፃር የተቃኘ መሆኑን የሚናገሩ ታዛቢዎች ጥቂት አይደሉም፡፡ ድርጅቱ የሚተገብራቸው ለሁሉም አገሮች ተመሳሳይ የሆኑ ህጎች የተለያዩ አገራትን የተለያየ የኢኮኖሚ ሁኔታ ያላገናዘበ መሆኑም ይተችበታል፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ የተፋለሱ አካሄዶች ናቸው እንግዲህ የአለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ይበልጣል የሚሉ ድምፆች እንዲሰሙ ያደረጋቸው፡፡

እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ከ1997 ጀምሮ ኢትዮጵያ አባል ሳትሆን በተሳታፊነት ደረጃ በስብሰባዎች ላይ ስትገኝ ቆይታለች፡፡ ምንም እንኳን ከስድስት አመታት በኋላ በፈረንጆች 2003 አባል ለመሆን ብታመለክትም እስካሁን ግን አባል አይደለችም፡፡ በመካከሉም የአገራችን የአባልነት ሂደት ለሚቀጥሉት ስምንት አመታት ተቋርጦ እንደ ነበር ይታወሳል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ኢትዮጵያ የባንክና የቴሌኮም ሴክተሮችን ለግል ባለቤትነት ወይም ለሃገርም ውስጥ ሆነ ለውጭ ኢንቬስትመንት ክፍት እንድታደርግ በመጠየቋ ነበር፡፡ በቅርቡ በፈረንጆች አፕሪል 2024 በተካሄደ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ የንግድ ድርጅቱ አባል የምትመሆንበት ሂደት እንዲቀጥል ውይይት ተካሂዶ ጉዳዩ እንደገና ነፍስ ዘርቶ መንቀሳቀስ ጀምሯል፡፡ በቅርቡ የተደረገው ውይይት ለአምስተኛ ጊዜ የተደረገ ሲሆን በዚህም ወቅት አገራችን የአባልነት ጥያቄዋን እንደገፋችበት ተረጋግጧል፡፡ ውይይቱ እንደ ተለመደው አሁንም ካልተቋረጠ የረጅም ጊዜ ሂደቱ በስኬት ይቋጫል ተብሎ እየተጠበቀ ነው፡፡

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# Business Consultancy Service from Addis Chamber

Let Us Make it Come True



- Business Plan Preparation
- Strategic Plan Preparation
- Feasibility studies,
- Business Clinic, etc...


contact us:
Mexico Square, Chamber Building
+251-115155221, +251-11518055 ext 218
+251931558929
marketing@addischamber.com,
flijalem4@gmail.com
www.addischamber.com

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# ADDIS CHAMBER

Institute of Directors Ethiopia

***Development of effective board leadership and application of best practices in corporate governance***



## SERVICES FOR DIRECTORS

- Certification Program
- Training Program
- Board Evaluation
- Standards and Codes
- Consultancy and Advisory Service
- Access to Certified Directors' database
- Recommending candidate directors
- Peer networking and forums
- Research and advocacy
- Publication

Mexico Square, Chamber Building

. +251 115155221

lod.aaccsa@gmail.com
www.Addis chamber .com

# የግብርና ምርታማነትን ለመጨመር የስምምነት እርሻ (Contract Farming) መፍትሄ እንደሚሆን ተገለጸ

**በሙሉጌታ ጉደታ**

የስምምነት እርሻ ቀደም ባሉት ግዜአት በሃገራችን በባህላዊ መንገድ የሚተገበር ሲሆን በዘመናዊ መልኩ በህግ ተደግፎ ተግባራዊ መሆኑ የምርት መጠንን ለመጨመር እንደሚያስችል የአዲስ አበባ ንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለባለድርሻዎች ባዘጋጀው ስልጠና ላይ ተጠቅሷል።

ስልጠናው የአትክልት እና ፍራፍሬ ምርቶችን በስምምነት እርሻ(Contract Farming) በመደገፍ ምርታማነታቸውን በመጨመር ረገድ ውጤታማነቱ እንዲሁም እንቅፋቶቹን የዳሰሰ ነው።
የስምምነት እርሻ ጽንሰ ሃሳብን እና በሌሎች ሃገሮች ያለውን ተሞክሮ በማንሳት ስልጠናውን የሰጡት በማማከር ዘርፍ የተሰማሩት ዶ/ር በየነ ታደሰ ምንም እንኳ የስምምነት እርሻ ምርትን የመጨመር ፤የአነስተኛ ገበሬዎችን ገቢ የማሳደግ ፤የአቅርቦት እሴት ሰንሰለትን ለማሻሻል፤ የውጭ ንግድ መጠንን የማሳደግ፤የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ማድረግ እና የመበደር አቅምን የማሳደግ እድል የሚፈጥር ቢሆንም ዘርፉን ለመደገፍ የሚያስችል የብድር አቅርቦት ስላልተመቻቸለት እንቅፋት እንደሚገጥመው አንስተዋል።

የስምምነት እርሻ የገንዘብ አቅም ባለው የግሉ ዘርፍ እና አምርቼ ማን ይገዛኛል የሚል ስጋት ባለበት ገበሬ መካከል በህግ ማእቀፍ በመደገፍ በጋራ የሚሰሩበት ሂደት ሲሆን ፡ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በተለያዩ የፍራፍሬ ምርቶች ውጤት እየታየበት መሆኑ ተነስቷል ከነዚህም አቮካዶ፤ፓፓያ እና ሙዝ ተጠቃሽ ናቸው።
ለስምምነት እርሻ እንቅፋት ከሆነው የብድር አቅርቦት ባሻገር የመሰረተ ልማት አቅርቦት አለመሟላት፤ የገበሬዎች ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን የሚሉትም ተጠቅሰዋል። የስምምነት እርሻን ተግባራዊ ለማድረግ በገበሬዎች ዘንድ አሁን አሁን ፍላጎቶች እየታዩ ቢሆንም በገበያው ላይ የሚታየው የዋጋ መቀያየር ገበሬዎችን ደፍረው እንዳይገቡ እንቅፋት እየሆነባቸው መሆኑን ያነሱት ሌላው አሰልጣኝ ከግብርና ሚኒስቴር የመጡት አቶ ሱልጣን መሃመድ ሲሆኑ ለስምምነት እርሻ የወጣው አዋጅ መሰል ስጋቶችን መቅረፍ የሚችል እና ከምርት በኋላ ለሚኖር የዋጋ ልዩነት በስምምነት መሻሻል እንደሚችል ጠቁመዋል።

በስምምነት እርሻ ውስጥ የዋጋ፡ የአከፋፈል ሁኔታ፡ጥራትን፡መጠንን እና ቀንን የሚያካትት መሆኑ በአምራች እና በአስመራች መካከል በሚደረግ ህግን መሰረት ባደረገ ውል ጥራት ያለው ምርት እንዲመረት እና ከሃገር ውስጥ አልፎ የውጭ ገበያን የሚያሟላ ምርት ማምረት እንደሚያስችል ተጠቅሷል።

በስልጠናው ማጠቃለያ እንደተጠቀሰው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው የስምምነት እርሻ በሌሎች ሃገሮች ያስገኘውን ውጤት በሃገራችንም ለማየት የመንግስት ድጋፍ እና መተማመን አስፈላጊ ናቸውም ተብሏል።

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER




አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER